የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች ህብረት (ኢሰመድህ)

**Consortium of Ethiopian Human Rights Organizations (CEHRO)**

*June 17, 2026 | Press Release*

*Addis Ababa*

## Statement on Election Day Observation Findings of the 7th General Election

The Consortium of Ethiopian Human Rights Organizations (CEHRO) conducted an Election Day observation of the Ethiopian 7th General Election on 1 June 2026. The observation mission was undertaken by deploying 19 mobile observers to 79 polling stations in Somali, Amhara, and Benshishangul-Gumuz Regions, focusing on locations hosting internally displaced persons (IDPs), as well as in Addis Ababa.

In addition, CEHRO deployed mobile observers to Special Polling Stations and conducted an Election Day observation on 9 June 2026, which covered the pre-voting, voting, and vote counting process. The observation was carried out in Bambasi IDP camps (Assosa Zone, Benishangul-Gumuz Region) and at the Special Polling Stations located in South Wollo Zone, Amhara Region.

**Positive Aspects**

CEHRO observed and encouraged the following positive aspects during the 7th General Election (1 June 2026).

- High-level collaboration from election officials for observers throughout the election day;
- Active engagement and responses from NEBE election coordinators to ensure the availability of essential election materials.
- In most polling stations, the voting process commenced at 6:00 a.m., and election officials were present at the polling stations before the commencement of voting and prepared the election materials;
- Voters reached at polling stations before the commencement of the voting process, which demonstrates an encouraging and active engagement of voters in the election process;

- Orderly queue management, accessibility of polling stations, and priority given for PWDs, the elderly, and pregnant women to vote;
- Availability of sufficient election materials at the polling stations; and
- Transparent voter identification and verification process.

**Areas that need improvement**

CEHRO's election day observation findings reveal the following areas of concern;

- Delayed commencement of voting process in some polling stations;
- Violation of secret ballot in some polling stations through marking ballots by election officials;
- Election officials frequently join voters in the secrecy booth and provide frequent support for voters without an express request from voters.
- Two or more voters mark their ballots at the same time within the same secrecy booth;
- It was observed that underage voters holding a voter identification card were allowed to vote on behalf of their parents, and the election officials assisted them in marking ballots.
- Unauthorized individuals (who were not election officials, voters, political parties' agents, or observers) were observed inside polling stations providing instructions to voters on how to mark their ballots, including within the voting secrecy booth. Despite this occurrence, the election officials failed to take necessary measures, and
- Observers and political party agents were directly counting votes and identifying valid and invalid ballots.

**Observation Findings from Special Polling Stations (SPS)**

CEHRO's observation indicates that the voting process across the observed Special Polling Stations (SPS) was conducted peacefully, with ample space for IDPs to engage in the democratic process, reflecting a positive step towards inclusive electoral participation. However, the observation findings also indicate the following limitations.

- Lack of sufficient and timely information from NEBE on the date of election at SPS, the number and location of SPS, which hinders CEHRO from actively engaging and deploying its observers;
- Limitation of information for voters about the date of the election, and voters in some Special Polling Stations were informed about it one day before the election day;
- Absence of accredited media and lack of media coverage of the voting process in the observed Special Polling Stations;
- Insufficient space for voters in the Special Polling Stations to cast their vote in the secrecy booth;
- Frequent support and presence of the election officials while the voters mark their ballot within the secrecy booth;
- Inconsistencies in the criteria for the establishment of Special Polling Stations (while IDP camps with a higher number of residents (like, for example, Degan IDP camps) do not have Special Polling Stations, in other areas, camps with fewer IDPs (like, for example, Kutaber and Gerado IDP camps) have been prioritized for SPS placement;
- Lack of interest among IDPs in voting for candidates from their areas of origin/displacement;
- Low voter engagement among IDPs (in Gerado and Kutaber IDPs camps), which was also documented in CEHROs' pre-election observation findings that voters' participation was driven by fear of repercussions rather than civic motivation. In addition, separate election days in Special Polling Stations create the perception of inequality among IDPs and reduce the visibility of the election process for national and international observers.

**CEHRO's Recommendations**

In light of CEHRO's pre-election and election day (conducted on 1 June 2026 and 9 June 2026) observation findings, we recommend that the observed positive aspects should be preserved and further strengthened in future elections. Furthermore, the challenges identified should be addressed in subsequent electoral processes and in post-election legal and procedural reforms.

ሰኔ 10፣ 2018 ዓ.ም፣

አዲስ አበባ

**<u>የ7ኛው ጠቅላላ ምርጫ የድምጽ መስጠት ሂደት ትዝብት ግኝቶችን አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ</u>**

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች ህብረት (ኢሰመድህ)፣ ግንቦት 24 ቀን 2018 ዓ.ም በተካሄደው 7ኛው ጠቅላላ ምርጫ ድምጽ በሚሰጥበት ዕለት የነበረውን የድምጽ አሰጣጥ ሂደት ታዝቧል። የምርጫ መታዘብ ተግባሩ አዲስ አበባን ጨምሮ፣ሶማሌ፣ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ እና አማራ ክልሎች ውስጥ በሚገኙ የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች ባሉባቸው ቦታዎች ላይ በማተኮር በ79 የምርጫ ጣቢያዎች 19 ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎችን በማሰማራት የተከናወነ ነው።

በተጨማሪም፣ ኢሰመድህ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ ክልል በአሶሳ ዞን (በባምባሲ የተፈናቃዮች መኖሪያ ካምፖች)፣ እንዲሁም በአማራ ክልል፥ በደቡብ ወሎ ዞን በሚገኙ ልዩ የምርጫ ጣቢያዎች ሰኔ 2 ቀን 2018 ዓ.ም. በተካሄደው 7ኛው ጠቅላላ ምርጫ ላይ ተንቀሳቃሽ የምርጫ ታዛቢዎችን በማሰማራት ድምጽ ከመስጠት በፊት፣ ድምጽ የመስጠት እና የቆጠራ ሂደቶችን መታዘብ ተችሏል።

## አዎንታዊ ጎኖች

ኢሰመድህ በ7ኛው ጠቅላላ ምርጫ የድምጽ መስጫ ቀን (ግንቦት 24 ቀን 2018 ዓ.ም) የሚከተሉትን አበረታች የድምጽ አሰጣጥ ሂደቶችን መታዘብ ችሏል፡፡

- የምርጫ አስፈፃሚዎች ምርጫውን ለመታዘብ ለመጡ ታዛቢዎች መልካም እና ቀና ትብብር ማድረግ መቻላቸው፤
- የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫ አስተባባሪዎች በየምርጫ ጣቢያዎች አስፈላጊ የምርጫ ቁሳቁሶች እንዳይጎሉ ያደረጉት ክትትል እና ድጋፍ፤
- በአብዛኞቹ የምርጫ ጣቢያዎች ድምጽ የመስጠት ሂደት ከጠዋቱ 12፡00 ሰዓት መጀመሩ እና የምርጫ አስፈፃሚዎች ድምጽ የመስጠት ሂደት ከመጀመሩ አስቀድመው በምርጫ ጣቢያ በመገኘት የምርጫ ቁሳቁሶችን በተገቢው መንገድ ማዘጋጀት መቻላቸው፤
- መራጮች የድምጽ መስጠት ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት በምርጫ ጣቢያዎች ቀድመው በመገኘት በምርጫ ሂደት ንቁ እና አበረታች ተሳትፎ ማሳየታቸው፤
- የምርጫ ጣቢያዎች ለአካል ጉዳተኞች፣ አረጋዊያን እና ነፍሰጡር/ልጅ ለያዙ ሴቶች ተደራሽ መሆናቸው፤ የተደራጀ የመራጮች ሰልፍ መኖሩ እና የምርጫ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት እንዲመርጡ ቅድሚያ ሊሰጣቸው ለሚገቡ መራጮች ቅድሚያ መሰጠቱ፤
- በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ ቁሳቁሶች እጥረት አለማጋጠሙ፤ እና
- ግልጽ የመራጮች መለያ እና ማረጋገጫ ሂደት በምርጫ አስፈፃሚዎች መከናወኑ ናቸው።

**ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች**

በኢሰመድህ የምርጫ ቀን የትዝብት ግኝቶች የሚከተሉትን ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች መታዘብ ችሏል፡፡

- በአንዳንድ የምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ መስጠት ሂደት ዘግይቶ መጀመሩ፤
- የምርጫ አስፈፃሚዎች በአንዳንድ የምርጫ ጣቢያዎች በመራጮች የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ላይ ምልክት ሲያደርጉ መስተዋላቸው፤
- የምርጫ አስፈፃሚዎች ያለ መራጮች ግልጽ የድጋፍ ጥያቄ በተደጋጋሚ ወደ ምስጢር ድምፅ መስጫ ቦታ በመግባት ለመራጮች ድጋፍ መስጠታቸው፤
- ከሁለት በላይ መራጮች በአንድ ጊዜ በአንድ የምስጢር ድምፅ መስጫ ቦታ ውስጥ ድምፃቸውን መስጠታቸው፤
- ከ18 አመት በታች የሆኑ ልጆች የመራጭነት ካርድ በመያዝ ቤተሰቦቻቸውን ወክለው እንዲመርጡ መደረጉ እና ለእነዚህ ልጆችም የምርጫ አስፈፃሚዎች በድምጽ መስጫ ወረቀቱ ላይ ምልክት ሲያደርጉ መስተዋሉ፤
- በምርጫ ጣቢያው ውስጥ እንዲገቡ የማይፈቀድላቸው ግለሰቦች (የምርጫ አስፈፃሚዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች፣ ታዛቢዎች እና መራጮች ያልሆኑ ግለሰቦች) በምርጫ ጣቢያው ውስጥ በመገኘት ለመራጮች ድምጽ እንዴት መስጠት እንዳለባቸው መመሪያ ሲሰጡ እና ከመራጮች ጋር በሚስጥር ድምጽ መስጫ ቦታ ላይ መገኘታቸው፣ ይህም ሲሆን የምርጫ አስፈፃሚዎች ተገቢውን እርምጃ አለመውሰዳቸው፤ እና
- የምርጫ ታዛቢዎችና የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች የድምጽ ቆጠራ ሲያካሂዱና ዋጋ ያላቸው/የሌላቸው ድምጾችን ሲለዩ መስተዋላቸው ናቸው፡፡

**በልዩ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች (SPS) የትዝብት ግኝቶች**

የኢሰመድህ የምርጫ ትዝብት እና የምርጫ ክትትል ግኝቶች ለሃገር ውስጥ ተፈናቃዮች በተቋቋሙ ልዩ ምርጫ ጣቢያዎች የተካሔደው የድምጽ አሰጣጥ ሂደት በሰላም መካሄዱን እና ለሃገር ውስጥ ተፈናቃዮች (IDPs) በዴሞክራሲ ሂደት ውስጥ መሳተፍ እንዲችሉ ያስቻለ እንዲሁም አካታች የምርጫ ተሳትፎን የሚያበረታታ አዎንታዊ እርምጃ መሆኑን መታዘብ ችሏል፡፡

ሆኖም በልዩ ምርጫ ጣቢያዎች የተከናወኑ የትዝብት ግኝቶች የሚከተሉት ተግዳሮቶች እንደነበሩ መመልከት ተችሏል፡-

- በልዩ የምርጫ ጣቢያዎች የሚካሔደው የድምጽ መስጠት ሂደት መቼ እንደሚካሔድ እና ልዩ የምርጫ ጣቢያዎች የተቋቋሙባቸውን ቦታዎች እና ብዛት የሚመለከቱ መረጃዎች ቀድመው ይፋ ባለመደረጋቸው ኢሰመድህ የምርጫ መታዘብ እና የክትትል ሂደቱ ላይ በሚፈለገው መጠን ለመሳተፍ እና ታዛቢዎችን ለማሰማራት እንቅፋት መሆኑ፤
- ለመራጮች ምርጫ የሚካሔድበትን ቀን አስመልክቶ በቂ መረጃ ባለመሰጠቱ በአንዳንድ ልዩ የምርጫ ጣቢያዎች የተመዘገቡ መራጮች ምርጫ መኖሩን ያወቁት ከምርጫው ቀን አንድ ቀን ቀደም ብሎ መሆኑ፤

- የምርጫ ትዝብት በተከናወነባቸው ልዩ የምርጫ ጣቢያዎች የተካሔደውን የድምጽ አሰጣጥ ሂደት አስመልክቶ ዘገባ የሚሰሩ ሚዲያዎች አለመኖር እና በቂ የሚዲያ ሽፋን አለማግኘቱ፤
- በምስጢር ድምፅ መስጫ ቦታ ውስጥ ድምፅ ለመስጠት በልዩ የምርጫ ጣቢያው ውስጥ በቂ ቦታ ለመራጮች አለመኖሩ፤
- መራጮች ድምፃቸውን ሲሰጡ በምስጢር ድምፅ መስጫ ቦታ ውስጥ የምርጫ አስፈፃሚዎች ተደጋጋሚ ድጋፍ መስጠታቸው እና በሚስጥር ድምፅ መስጫ ውስጥ ከመራጮች ጋር መስተዋላቸው፤
- ልዩ የምርጫ ጣቢያዎች ሲቋቋሙ ወጥነት ያለው መስፈርት አለመከተላቸው፤ በአንዳንድ ከፍተኛ የአገር ውስጥ ተፈናቃይ ቁጥር ባለባቸው ቦታዎች (ለምሳሌ በደጋን የሃገር ውስጥ ተፈናቃዮች መኖሪያ ካንፕ) ልዩ የምርጫ ጣቢያዎች ሳይቋቋሙ ልዩ የምርጫ ጣቢያዎች ትንሽ ቁጠር ባለባቸው ካንፖች (ለምሳሌ በኩታበር እና ገራዶ የሃገር ውስጥ ተፈናቃዮች መኖሪያ ካንፖች) ውስጥ ልዩ የምርጫ ጣቢያዎች መቋቋማቸው፤
- መራጮች ከቀድሞ አካባቢያቸው ወይም ከተፈናቀሉበት ክልል የሚወዳደሩ እጩዎችን ለመምረጥ ዝቅተኛ ፍላጎት ማሳየታቸው፤
- በገራዶ እና በኩታበር የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች መኖሪያ  ካምፖች ዝቅተኛ የመራጮች ተሳትፎ መታየቱ እና ይህም ኢሰመድህ ካደረጋቸው የቅድመ-ምርጫ ክትትል ግኝቶች መካከል መራጮች ድምጽ ለመስጠት በልዩ ምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ የተገኙት ካልመረጥን የሚመጣብን ችግር ይኖራል የሚል ስጋት መኖሩን መረዳቱ፤ እና በመደበኛ የምርጫ ጣቢያዎች እና በልዩ የምርጫ ጣቢያዎች የተካሔደው የምርጫ ቀን መለያየት በመራጮች ዘንድ ድምፃቸው በቂ ትኩረት እንዳልተሰጠው እና ከእኩልነት መርህ ጋር የሚጋጭ እንደሆነ እንዲሰማቸው ማድረጉ ናቸው

**የኢሰመድህ ምክረ-ሀሳቦች**

ኢሰመድህ ባደረጋቸው የቅድመ-ምርጫ ክትትል፥ የምርጫ ቀን ትዝብት (ግንቦት 24 ቀን 2018 ዓ.ም እና ሰኔ 2 ቀን 2018 ዓ.ም) ግኝቶች መሰረት በጠንካራ ጎናቸው የታዘብናቸው ጉዳዮች በቀጣይ ምርጫዎች ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው  እና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች በቀጣይ የምርጫ ሂደቶች እና በድህረ ምርጫ የህግጋትና የአሰራር ሪፎርሞች  ትኩረት ተደርጎባቸው ሊሻሻሉ እንደሚገባ ማሳሰብ ይወዳል።


**ለተጨማሪ መረጃ**

**ኢሜል**: info@cehro.org **ወይም** cehro2010@gmail.com

**ድህረ ገጽ** : www.cehro.org

**ስልክ ቁጥር:** +251 116-67-00-97